# ለህዝብ ፍላጎት ጆሯችሁን ስጡ!

ዳዊት አጥናፉ (ከአየር ጤና)

የሕዝብን ጥቅም፣ ፍላጎትና ሁለንተናዊ መብቶች መሰረት አድርጎ የሚቀረፅ ህገ መንግስት ለውጤታማና ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መሰረት ነው፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ስርዓት የታደለ ማህበረሰብ ከልዩነት ይልቅ አንድነትን ያጠናክራል፣ ከፍተኛ አገራዊ ፍቅርን ይላበሳል፣ በብሄር፣ በቋንቋና በባህል የተለያየ ቢሆንም እንኳ በመካከሉ ልዩ የሆነ መተማመንንና በጋራ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ አንድነትን ይገነባል፡፡

ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የተገነዘበና በእርሱም እምነቱን ያሳደረ ማህበረሰብ በሚኖርባቸው አገራት ውስጥ የሚከሰቱ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለአመጽና ለእርስ በእርስ ግጭት ምክንያት አይሆኑም፡፡

ስርዓቱ በማህበረሰቦች መካከል የላቀ መተማመንና መተሳሰብን የሚያስከትል በመሆኑ ለሚፈጠሩት ፈተናዎች አንዱ በሌላው ላይ ጣቱን አይቀስርም፡፡ ከዚህ ይልቅ ፍፁም በሆነ የመተማመንና የመግባባት መንፈስ ማህበረሰቦቹ ለሚገጥሟቸው ችግሮችና ፈተናዎች መፍትሄውን ለማበጀት የሚቻላቸውን ሁሉ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

የዚህ ዓይነቱ ማህበረሰብ የሚመራውን መንግስት ለስልጣን የሚያበቃው በምርጫው በመሆኑ በመንግስቱ ላይም ከፍተኛ እምነትን ይፈጥራል፡፡ ይህም በአገሪቱ ጠንካራ ሰላምና መረጋጋት እንደዚሁም ብሩህ የሆነ የእድገትና ለውጥ ራእይ እንዲኖር፣ ራእዩም በተገቢው መጠንና ፍጥነት እውን እንዲሆን የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በአጠቃላይ አገሪቱ በእኩልነት፣ በፍትህና በጋራ ጥቅም ላይ ጠንካራ እምነት ያለው ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ የሚመራት ትሆናለች፡፡

በተቃራኒው ዴሞክራሲያዊ እሳቤን መሰረት አድርገው የተቋቋሙ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ተቋማት በሌሉባቸው አገራት ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የተላበሰ ማህበረሰብ ማግኘት በእጅጉ ያዳግታል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በሚታይባቸው አገራት የህዝቦችን የፖለቲካና ኢኮኖሚ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ስርዓት ባለው መልኩ ማስተናገድ ስለሚሳን በህዝቦች እና መንግስታት መካከል ብቻ ሳይሆን በተለያዩት የህብረተሰብ ክፍሎች ጭምር ሁሌም የከፋ ጥርጣሬና አለመተማመን አለ፡፡

በእነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ የሕዝብ ምሬትና ሮሮ ምን ጊዜም አይጠፋም፡፡ ምሬት፣ ቂምና ጥርጣሬ በነገሰበት ማህበረሰብ ውስጥ ደግሞ ምንም ዓይነት የተፈጥሮ ኃብት ክምችት ቢኖር እንኳ የሕዝብን ህይወት ሊያሻሽል የሚችል የኢኮኖሚ እድገት አይታሰብም፡፡ መንግስታቱ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ የልማት እቅድ ለመተግበር ቢሞክሩም እንኳ የሕዝብ ድጋፍ የራቃቸው በመሆኑ ደካሞች ናቸው፡፡

በእነዚህ ዓይነቶቹ አገራት ውስጥ ዘውትር ስጋት አለ፤ ሰላምና መረጋጋት የለም፡፡ እንዲያውም ብዙዎቹ ወደእርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ድህነትና ችጋር እየጨመረ እንጂ ሲቀንስ አይታይም፡፡ ስደት፣ ርሃብና መሰል ማህበራዊ ቀውሶች የእነዚህ አካባቢዎች ዋነኛ መገለጫዎች ይሆናሉ፡፡

ማህበራዊ ቀውሱ በዓይን የማይታው እንኳ ቢሆን የዚህ ዓይነቶቹ አገራት ህዝቦች የታመቀ ምሬትና ብሶት ይኖርባቸዋል፡፡ በመሆኑም በሆነ አንድ መጥፎ አጋጣሚ ይህ የሕዝብ ምሬት ገንፍሎ በማህበረሰቡ ውስጥ የከፋ ስርዓት አልበኝነት፣ የእርስ በርስ ግጭትና ደም መፋሰስ ይከሰታል፡፡

የዚህ ዓይነቱ የታሪክ ክስተት በተለያዩ የአፍሪካና ሌሎች አገራት ውስጥ ታይቷል፤ በመታየት ላይም ይገኛል፡፡ የመካከለኛው ምስራቅና የሰሜን አፍሪካን ሁኔታ ለዚህ አብነት አድርጎ ማንሳት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት በተወሰነ ደረጃ እየቀነሰ ቢመጣም በተለይ በእኛዋ የአፍሪካ አህጉር መሪዎች በድንገት ሲሞቱ ወይም ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ሲፈፀም የምናየው ደም መፋሰስና የሰብአዊ ቀውስ ተጨማሪ ማሳያ ይሆናል፡፡

ኢትዮጵያዊያን በተለይ ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ጀምሮ በተለየ የፖለቲካና ኢኮኖሚ መዋቅር ውስጥ መኖር ጀምረዋል፡፡ ከአገሪቱንና ዜጎቿን ለዚህ የተለየ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት ያደላት ደግሞ ከአገር አልፎ ዓለም አቀፍ የፖለቲካና ማህበረሰባዊ ሳይንስ ምሁራን ሳይቀሩ ባደነቁት ህገ መንግስት አማካኝነት ነው፡፡

ይህ ህገ መንግስት አገሪቱ ከተመራችባቸው ቀደምት ህገ መንግስቶች የሚለይበት ዋናው ቁም ነገር ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የአገሪቱ ባለቤቶች፣ አድራጊና ፈራጆች እንዲሆኑ ሙሉ መብት መስጠቱ ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያዊያ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ስርዓት ቀደምት የአገሪቱ ገዢዎች አፍነውትና ረግጠውት ለኖቱት የዘመናት የህዝቦች የመብት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ሰጥቷል፡፡

ይህንንም መብቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ የሚችሉበትን የፌዴራላዊ ስርዓት እንዲገነቡ፣ በዚህም አማካኝነት የአገሪቱ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር መቻላቸውና ከአገሪቱ ኃብትም ፍትሃዊ ተጋሪነታቸው እንዲረጋገጥ አድርጓል፡፡ እነዚህ የህገ መንግስቱ ዓይነተኛ ገፅታዎች በአገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ ሰላምና መረጋጋትን አምጥተዋል፤ ለዘመናት በጎሪጥ ሲተያይ በኖረው ህዝብ መካከልም መተማመንንና አንድነትን ፈጥሯል፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ ከአንድ ዓመት በፊት ተካሂዶ በነበረ ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ የቀረበ አንድ ጥናት እንዳመለከተው በኢትዮጵያዊያ የአሁኑ ፌዴራላዊ የፖለቲካ ስርዓት ባይመሰረት ኖሮ የዛሬዋ ኢትዮጵያዊያ ላትኖር ትችል ነበር፤ ይህችን አገር ከመበታተን ያዳናትና ለዛሬው የለውጥ ጎዳና ያበቃት በህዝቦች ይሁንታ የተቀረፀው ህገ መንግስትና እርሱን ተከትሎ የተመሰረተው የፌዴራል ፖለቲካ ስርዓት ነው፡፡

ህገ መንግስቱና የፌደራል ስርዓቱ አገሪቱን በመለወጥ ላይ ነው፡፡ ይህንን የተገነዘቡት የኢትዮጵያዊያን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የስርዓቱ ጠበቃና አለኝታ መሆናቸውን በተግባር ማሳየት ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

በአገራችን ከመለስ ህልፈት ጋር በተያያዘ ሰሞኑን የተስተዋለው የፖለቲካ ክስተት ያረጋገጠው ይህንን ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ተቃዋሚዎችና በሰብአዊ መብት ጥበቃ ስም የአገራችንን ስም የሚያጎድፉት አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማት የተነበዩት ብጥብጥ የአገሪቱንና የህዝቦቿን ተጨባጭ ሁኔታ ካለመገንዘብ ያሴሩት የፖለቲካ ሴራ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

በኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ያለው ህዝብ መብቶቹ የተረገጡበት፣ በምሬት የተሞላና በሆነ አንዳች አጋጣሚ ለአመፅ የሚነሳ አይደለም፡፡ የአሁኑ ነባራዊ የኢትዮጵያ ሁኔታ ፅንፈኛ የሆኑት አንዳንድ ተቃዋሚዎችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ከሚያስቡት ፍፁም የተራራቀ ነው፡፡

የታላቁ መሪያችን መለስ ህልፈት በአገራችን ብጥብጥንና የእርስ በእርስ ግጭትን ያስነሳል የሚል በርካታ መላ ምት ሲቀርብ ሰንብቷል፡፡ በጥቂት ፅንፈኛ ፖለቲከኞችና አንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማት አማካኝነት ሲቀርብ የነበረው ይህ መላምት ዛሬ ባዶ ሆኗል፡፡

ከመለስ ህልፈት ዜና ቀን ጀምሮ ህዝቡም ሆነ መንግስት በበለጠ መረጋጋትና ሰላም የተለመደውን ተግባራቸውን ሲከውኑ አልፈዋል፡፡ የመለስ ስርዓተ ቀብር በታላቅ ክብር ተከናውኗል፡፡ አገሪቱም አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር መርጣለች፡፡ በአሁኑ ወቅትም የተለመደው መንግስታዊ ተግባር በተለመደው መንገድ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ አሁን ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ ካለፉ ሁለት ወር ሊሞላው የቀሩት ጥቂት ቀናት ብቻ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ አንድ መሪ ህዝባዊነት በተላበሰ ስነ-ስርዓት መሪውን በክብር ሲሸኝ ይህ የመጀመሪያው እንደሆነ ይነገራል፡፡ በዚህ ስርዓተ ቀብር ላይ የተለያዩ አገራት መሪዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ኃላፊዎች መገኘታቸው በራሱ ለክስተቱ ልዩ ትርጉምን ያጎናጽፈዋል፡፡

የመሰል ስርዓተ ቀብር በሰላምና እጅግ የህዝብ ወገንተኝነት በተንፀባረቀበት መልኩ ሊፈፀም የቻለው መለስ የመሩት መንግስትና የፖለቲካ ኢኮኖሚ ስርዓት ውጤታማና ትክክለኛ ስለነበር መሆኑን ያሳያል፡፡

ከመለስ ህልፈት ጋር በተያያዘ ያስተዋልነው ሐቅ በኢትዮጵያ የሕዝብን ጥቅም፣ ፍላጎትና ሁለንተናዊ መብቶች መሰረት ያደረገን ህገ መንግስት ተከትሎ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመገንባት ላይ መሆኑንና ይህም ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብን የተገነዘበና በእርሱም እምነቱን ያሳደረ ማህበረሰብ በመፍጠር ላይ መሆኑን ነው፡፡

ከዚሁ ጋርም የመለስ ህልፈትን ተከትሎ በአገራችን የተስተናገደው ክስተት በማህበረሰቡ ውስጥ ጠንካራ የመተማመንና የመግባባት መንፈስ መጎልበቱንም ጭምር ያረጋገጠ ነው፡፡

እናም ትንበያው ከጭፍን የፖለቲካ ፍላጎት የመነጨ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ሆኗል፡፡ አገራችን በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊባል በሚችል መልኩ በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ እየበለፀገ የመጣ ማህበረሰብን ማየት ጀምራለች፡፡ አያሌ ዓመታትን የፈጀ መስዋእትነትን ተከትሎ ተግባራዊ የሆነው የአገሪቱ ህገ መንግስትና ይህንኑ መሰረት በማድረግ የተዋቀረው ዴሞክራሲያዊ የፌዴራል ስርዓት በሕዝቡ ውስጥ ጠንካራ መተማመንንና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ አንድነትን ፈጥሯል፡፡

ስርዓቱ ከሀያ ዓመት በፊት አንዳችም ትኩረት ሳይሰጣቸው ለኖሩት የአገሪቱ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ሙሉ እውቅናን እንደዚሁም እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ መብት ማጎናፀፉና ሁሉም ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የአገሪቱን ኃብት እንዲካፈሉ ማድረጉ አገሪቱ በዓለም የሚጠቀስ ሰላምና ልማት እንድታስመዘግብ አስችሏታል፡፡

ባለፉት ሀያ ዓመታት ጊዜ ውስጥ እየተጠናከረ የመጣው ሰላምና እድገት በዜጎች ልብ ውስጥ ከፍተኛ የለውጥ ተስፋ እንዲጎመራ አስችሏል፡፡ ስርዓቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን ከድህነት ለማውጣት ያስቻለ ከመሆኑም በላይ የአገሪቱ መጠሪያ ሆኖ የኖረውን ድህነት ታሪክ ለማድረግ ከፍተኛ መነቃቃትንና ወኔን ፈጥሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የሚታየው የልማት እድገት አመርቂና ተስፋ ሰጪ መሆኑን የዓለምን የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚከታተሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር ምስክርነታቸውን በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ የተዘረጋው የፖለቲካ ኢኮኖሚ ስርዓት ድህነትን በመዋጋት ረገድ እያሳየ ያለው ውጤት የሚያበረታታ መሆኑን የአገሪቱ የልማት አጋር የሆኑ የበለፀጉ አገራትና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ሁሉ በመግለፅ ላይ ናቸው፡፡

በተለይ በስልጣን ላይ የሚገኘው መንግስት ከተለያዩ አካላት በብድርና በድጋፍ መልክ የሚያገኘውን ገንዘብ ለተገቢው ዓላማ በተገቢው መንገድ በማዋሉ አድናቆትን አትርፏል፡፡ ይህም እነዚህ አካላት የሚሰጡትን ድጋፍ የበለጠ አጠናክረው እንዲቀጥሉበት እያበረታታቸው እንደሚገኝ አካላቱ በራሳቸው አንደበት በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገልፁ ይሰማል፡፡

የመለስ ህልፈትን ተከትሎ በአገሪቱ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የስልጣን ሽግግር በመካሄዱም የአገሪቱ ወዳጅ የሆኑ አገራትና ዓለም አቀፍ ተቋማት አድናቆታቸውን ገልፀዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞም ከአገሪቱ ጋር ያላቸውን የትብብር ግንኙነት የበለጠ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ቃል ገብተዋል፡፡

መለስ ካለፉ አሁን ሁለት ወር ሊቆጠር ጥቂት ቀናት ቀርተውታል፡፡ በአገሪቱም የተለመደው የእለት ተእለት ተግባር በተጠናከረ መልኩ ቀጥሏል፡፡ የአገሪቱ የልማት አጋሮችም በቃላቸው መሰረት የተለመደውን የልማት ትብብራቸውን ቀጥለዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት የዓለም ባንክ የዳይሬክተሮች ቦርድ በኢትዮጵያ ለሚካሄደው የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም የሚውል የ1 ነጥብ 15 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከወለድ ነፃ ብድር ማፅደቁ የሚያበረታታ ተግባር ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ከዚሁ ብድር ውስጥ 600 ሚሊዮን ዶላር የሚሆነው ትምህርትንና ጤናን ለመሳሰሉ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ የሚውል ነው፡፡ ቀሪው ደግሞ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው የሚባሉ አምስት መንገዶችን በተሻሻለ ሁኔታ ለመገንባት የሚውል መሆኑም ተመልክቷል፡፡

ባንኩ ባወጣው መግለጫ መሰረት ለኢትዮጵያ መንግስት የሚሰጠው ይህ ብድር የተገኘው ከአውሮፓ ህብረት፣ ከዩናይትድ ኪንግ ደም ዓለም አቀፍ የልማት ትብብርና ከአፍሪካ ልማት ባንክ እንደዚሁም ኢጣሊያንና ከአውስትራሊያን ከመሳሰሉ የልማት አጋሮቹ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዓለም ባንክ የሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተሮች ቦርድ ከኢትዮጵያ ጋር ባለፉት አምስት ዓመታት ያካሄደውን የልማት ትብብር በማደስ አዲስ የአጋርነት ስትራቴጂ መንደፉንም አስታውቋል፡፡

በመጪዎቹ አምስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ስራ ላይ የሚውለው ይህ የዓለም ባንክና የኢትዮጵያ መንግስት የልማት ትብብር ስትራቴጂ ትኩረት በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ እየተመዘገበ ያለውን ዕድገት ማስቀጠል ይሆናል፡፡ አዲሱ የትብብር ፕሮግራም የስራ እድል በመፍጠር፣ የጤናና ትምህርት አገልግሎቶችን በማሻሻል ላይ የሚያተኩሩ ናቸው ተብሏል፡፡

ከዓለም ባንክ ባሻገር በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ተረጂ የሆኑ ህዝቦችን ከተረጂነት ለማውጣት የሚያካሂደውን ፕሮግራም ለማጠናከር የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍም ተገኝቷል፡፡

የአሜሪካን መንግስት ከቡድን ስምንት አባል ሀገራት ጋር በመሆን በመጪዎቹ አስር አመት 50 ሚሊየን ያህል ከሰሀራ በታች አገራት ህዝቦችን ከተረጂነት ለማውጣት እና 15 ሚሊየን ህፃናትን ከተመጣጠነ ምግብ አጥረት ለመታደግ አዲስ እቅድ ነድፏል፡፡

በአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ አነሳሽነት በግንቦት ወር የተጀመረው የዚህ እቅድ የመጀመሪያዎቹ ተጠቃሚ አገራት ኢትዮጵያ፣ ታንዛንያና ጋና መሆናቸውን ባለፈው ሳምንት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ዘግበዋል፡፡

የአሜሪካ መንግስት የምግብ ዋስትና ቢሮ ምክትል ሀላፊ ፓውል ዌይሴንፌለድ ሰሞኑን እንደገለፁት የቡድን ስምንት ሀገራት በቅርቡ የአፍሪካን የግብርና ምርት ለማሻሻል ቃል ከገቡት 18 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ኢትዮጵያ ተጠቃሚ ትሆናለች፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት መሟላት የሚገባውን የትብብር መስፈርቶች ማሟላቱን ምክትል ኃላፊው አስታውቀዋል። በተለይም የኢትዮጵያ መንግስት ለአርሶአደሩ ህዝብ የሰጠው የመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደ አንድ አበረታች መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ አገሪቱ ባለፉት ዓመታት ባስመዘገበችው ተከታታይ የኢኮኖሚ እድገት ምክንያት የተረጂዎች ቁጥር መቀነሱ የሚያበረታታ ተግባር መሆኑን ፓውል ዌይሴንፌለድ ጠቅሰዋል፡፡

ሌላው ባለፈው ሳምንት አገሪቱ ያገኘችው የልማት ድጋፍ ከቻይና መንግስት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በኢትዮጵያ ሁለት የስኳር ፋብሪካዎችን ለመገንባት የሚውል የ500 ሚሊዮን ዶላር ወይም የ8 ቢሊዮን ብር ብድር ከቻይና የልማት ባንክ ተገኝቷል፡፡

እነዚህ እንግዲህ ከመለስ ህልፈት በኋላ በዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ተነግረው የሰማናቸው ናቸው፡፡ ሌሎች በተለያየ መልኩ ለመንግስት የቀረቡ ሆኖም ግን ያልሰማናቸው የገንዘብ ድጋፎችና ቃል ኪዳኖች ሊኖሩ እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

ህይወታቸውን ሙሉ ለአገራችንና ህዝቦቿ መሻሻል የለፉት መለስ ዜናዊ ዜና እረፍት ከተሰማበት ጊዜ አንስቶ በተግባር የታየው እውነታ ኢትዮጵያ በከፍተኛ የለውጥ ሂደት ውስጥ መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ መላው ዜጋም ሆነ የአገራችን የልማት አጋር የሆኑ መንግስታትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ይህ የለውጥ ሂደት የበለጠ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያላቸውን ሙሉ እምነት ያሳያል፡፡

በአገሪቱ የአምስት ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ መሰረት የተለያዩ ግዙፍ የመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ በመካሄድ ላይ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ይህ የአገሪቱን የኢኮኖሚ መዋቅር ለመቀየር የሚያስችል መሰረት ይጥላል ተብሎ የሚጠበቀውን ብሄራዊ የልማት እቅድ የተለያዩ ባለፀጋ አገራትና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት በመደገፍ ላይ ናቸው፡፡

እነዚህ አካላት የመለስ ህልፈትን ተከትሎ በሰጧቸው መግለጫዎች ለእቅዱ ስኬት የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንደሚቀጥሉ ቃል ገብተዋል፡፡ ተተኪው የአገሪቱ መሪም በመለስ የተጀመሩትን የልማት ውጥኖች አጠናክሮ እንደሚቀጥል እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትራችን አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝና መንግስታቸውም በመለስ የስልጣን ዘመን የተጀመሩትን የልማት ውጥኖች እንደዚሁም መለስ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የተለያዩ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ጉዳዮች ውስጥ ያደርጉት የነበረውን የነቃ ተሳትፎ አጠናክሮ እንደሚቀጥሉ ይፋ አድርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ የልማት አጋር የሆኑት መንግስታትና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በመለስ የአመራር ዘመን የጀመሩትን የልማት ትብብርና ድጋፍ መቀጠላቸው በአገራችን ለውጥና ይህ ለውጥም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ሙሉ እምነት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው፡፡

ብዙዎቹ እነዚህ አካላት አቶ መለስ በህይወት በነበሩበት ጊዜ ለአገራቸውና ለዓለም ባበረከቱት አስተዋጽኦ በእጅጉ የተማረኩ ናቸው፡፡ በአገራችን ባለፉት 20 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በመሰረተ ልማት፣ በምግብ ዋስትና፣ በስራ እድል ፈጠራና በከተሞች ልማት የተከናወኑት ተግባራት የአገሪቱን ህዝብ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱ የልማት አጋር የሆኑትን ጭምር ያረካ ነው፡፡

በብዙዎች እምነት አገሪቱ ለዚህ ሁሉ የሚያኮራ ውጤት የበቃችው የመላውን ዜጋ እኩልነትና መብት ያጎናፀፈ፣ ብሄር፣ ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን ያቀራረበና ፍትሃዊነትን የተከለ የፌደራል ስርዓት በመገንባቷ ነው፡፡

ህዝቡ ከዚህ ስርዓት ያገኘውን ጥቅም ጠንቅቆ መረዳት ጀምሯል፡፡ ይህንን ስርዓት ለመገንባት መስዋእትነት ከከፈሉት ግንባር ቀደም የአገራችን ውድ ልጆች መካከል የሆኑት መለስ በሞት ሲያልፉ ከአገራችን ህዝብ የተንፀባረቀው የሀዘንና የቁጭት መንፈስ ህዝቡ ከስርዓቱ እያገኘ ያለውን ጥቅም ጠንቅቆ መረዳቱን በግልፅ አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ህዝቡ ይህንን ስርዓት ለመጋፋት የሚመጣ ምንም ዓይነት ኃይልን ለመጋፈጥ እንደማያቅማማ መገመት ለማንም አያዳግትም፡፡

ይህንን ስርዓት በማጣጣል የራሳቸውን የፖለቲካና ኢኮኖሚ ጥቅም ማስከበር የሚፈልጉት የአገራችን ተቃዋሚዎችም ሆኑ በሰብአዊ መብት ጥበቃ ስም የሚንቀሳቀሱ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ይህንን የህዝብ ስሜት ሊያከብሩ ይገባል፡፡

አብዛኛው የተቃዋሚው ጎራ ይህንን የህዝብ ስሜት ማዳመጥ ስለተሳነው ነው አሁንም ድረስ እጅግ በበዙ ችግሮች ውስጥ ተተብትቦ የሚገኘው፡፡ በአገራችን ከመለስ ህልፈት ጋር በተያያዘ ያስተናገድነው ድባብ ፅንፈኞቹ ተቃዋሚዎችና የአገራችን ህዝብ ምን ያህል የተራራቁ መሆኑን ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡

በአሁኑ ወቅት በምንኖርባት ኢትዮጵያ ያለው ሰላምና መረጋጋት የበለጠ እንዲጠናከር፣ በፍጥነት እያደገ የሚገኘው ኢኮኖሚ ዘላቂነት እንዲኖረው አስፈላጊው ሁኔታ እንዲመቻችባት ማድረግን እንጂ መለያየት፣ አመፅና ጥፋት የሚሰበክባት እንዳልሆነች ተቃዋሚዎች መገንዘብ አቅቷቸዋል፡፡

የአገራችን አንዳንድ ተቃዋሚዎች የህዝብን ስሜት በቅጡ ማዳመጥ ተስኗቸው ሳለ ፍጹም ጥንካሬንና ኃላፊነትን የሚጠይቀውን አገር የመምራት ህልም ማለማቸው የፖለቲካ ብቃታቸውን አፈር ድሜ የሚያስገባው ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ሁሌም ከራሳቸው ጋር እየተጣሉ የምናውቃቸው እነዚህ ኃይሎች የአገሪቱን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንም ቢሆን በወጉ የማያውቁ መሆናቸውን ጭምር ማንም ለማጤን አያዳግተውም፡፡

ከእነዚህ ተቃዋሚዎች በህጋዊ መንገድ ተደራጅተው መንቀሳቀስ ከጀመሩ 20 ዓመታትን ያሳለፉ ቢሆንም አሁንም ድረስ አንዳች ጥንካሬ አይስተዋልባቸውም፡፡ እነዚህ ኃይላት ከምንም ነገር በላይ አገርና ህዝብን ማስቀደም ከሚለው የተቀደሰ ዓላማ በላቀ የዘውትር ህልማቸው የግል ጥቅማቸውን የሚያስጠብቁበት ስልጣን ብቻ ነው፡፡

በውስጣቸው የሚታየው የዘውትር ውዝግብና ንትርክ ይህንንም ተከትሎ በመካከላቸው የሚፈጥሩት መከፋፈልና ባላንጣ ሆኖ መቀጠል ዋናው ምክንያት የስልጣን ሹክቻ መሆኑ ህልማቸው ስልጣን ብቻ መሆኑን ለማሳየት በቂ ማስረጃ ይመስለኛል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በተቃውሞ ጎራ ተሰልፈው የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ጋር ፍፁም ሊወዳደሩ አይችሉም፡፡ ኢህአዴግ ውስጣዊ ዴሞክራሲው ጠንካራና አገር መምራትን በሚያህል ታላቅ ኃላፊነት የተፈተነ ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ከመለስ ህልፈት ጋር በተያያዘ ገገርው ፓርቲ ውስጥ የስልጣን ሽኩቻ ይኖራል ብለው ያለሙትና የተመኙት ኢህአዴግን በእነርሱ መነፅር በማየታቸው ነው፡፡ ሆኖም ኢህአዴግ አንዳች አሉታዊ ድምፅ ባልተሰማበት ሁኔታ በሰላማዊ መንገድ የስልጣን ሽግግሩን በማካሄድ አዲስ ታሪክ ሰርቷል፡፡

ይህ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ዜናችን አኩርቷል፣ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማበብና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ከልባቸው የሚቆረቆሩ አገራትንና ዓለም አቀፍ አካላትን ጭምር በማስደሰትም ለአገራችን መልካም ገፅታ ግንባታ በዋጋ የማይሰላ ተጨማሪ እሴትን ፈጥሯል፡፡ በዚህም አማካኝነት ነው ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ከአገራችን ጋር ያለውን ወዳጅነትና የትብብር ግንኙነት አጠናክሮ እንደሚቀጥል በይፋ ያስታወቀው፣ ከወዲሁም ተግባራዊ ድጋፉን የቀጠለው፡፡

በአገራችን የተካሄደው የስልጣን ሽግግር ለሌሎች የአፍሪካ አገራት ጭምር ምሳሌ ሊሆን የሚገባው ተግባር መሆኑን ብዙዎች ገልፀዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት ተቃዋሚዎቻችንም ሆኑ አንዳንድ የአገራችን ስርዓት ጠላት የሆኑ ዓለም አቀፍ ተቋማት ከአገራችን ሁኔታ ብዙ ሊማሩና መስመራቸውን ሊያስተካክሉ ይገባ ነበር፡፡

ሆኖም ግን ለአንድም ጊዜ እንኳ የተሻለ ነገር ሲያደርጉ ታይተው የማያውቁት ተቃዋሚዎቻችን ከአገሪቱ ህዝብ ባለፈ በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጭምር ተቀባይነቱ እየተጠናከረ በመጣው መንግስት ላይ እርባና የሌለውን ወቀሳ መሰንዘራቸውንና ህዝቡንም ለጥፋትና ውድመት መቀስቀሳቸውን ገፍተውበታል፡፡

ይህ የጥፋት መስመር ትርፉ ድካም ብቻ መሆኑን ህዝቡ በተግባር እያሳየ ይገኛል፡፡ ህዝቡ ጽንፈኝነትንና ጥፋትን ለማስተናገድ ይቅርና ሊያዳምጥም ዝግጁ አለመሆኑን አረጋግጧል፡፡ ተቃዋሚዎቻችንም ሆናችሁ የሚያግዟችሁ ዓለም አቀፍ ተቋማት ይህንን የህዝብ ስሜት አሁን ካልተገነዘባችሁ መቼም ትልገነዘቡ አይቻላችሁም፡፡ ህዝቡ ያለአንዳች ማመንታት ፅንፈኝነትን አውግዟል፡፡ እናንተ ያላችሁ ብቸኛው እድል ለህዝብ ስሜትና ፍላጎት ጆሯችሁን መስጠት፣ በዚሁ የህዝብ ስሜትና ፍላጎት መሰረትም መንቀሳቀቀስ ብቻ ነው፡፡